# አጋርነት

ስዊዘርላንድ ውስጥ የተለያዩ ሰዎች በጋራ በአንድ ላይ ይኖራሉ። መጋባት ከፈለጉ ግን ዕድሜቻቸው ቢያንስ ቢያንስ 18 መሙላት አለበት። ሁለቱም የትዳር ጓደኞማቾች እኩል መብት አላቸው።

## በጋራ አንድ ላይ መኖር

ስዊዘርላንድ ባለፉት 10 ዓመታት ብዙ ለውጥ አሳይታለች። አብዛኛውን ግዜ ያልተጋቡ ጥንዶች (ሳይጋቡ እንደ ትዳር አብሮ መኖር፣ Konkubinat). በጋራ አንድ ላይ ይኖራሉ። ጥንዶቹ የጋራ ልጆች አላቸው። በጥንዶቹ/በአጋሮቹ/ መካከል ቋሚ የሆነ የስራ ክፍፍልና ድርሻ የለም። ይህም ማለት ሴቶችና ወንዶች ግንኙነታቸውን በሚመለከት የነጠረ የስራ ክፍፍልና ድርሻ የላቸውም፣ ይህም ማለት እነዚህ ሴቶች እና ወንዶች በግንኙነታቸው ውስጥ የተወሰኑ የስራ ክፍፍልና ድርሻ ማከናወን አያስፈልጋቸውም።
ተመሳሳይ ጾታ ያላቸው ጥንዶች በጋራ በአንድ ላይ መኖር ይችላሉ። ለምሳሌ ያህል፣ አንድ ወንድ ከአንድ ወንድ ጋር፣ ወይም አንዲት ሴት ከአንዲት ሴት ጋር ማለት ነው። እነሱም እንደ ሌሎች ጥንዶች እኩል መብት አላቸው፣ ከዚያም በላይ መጋባትም ይፈቀድላቸዋል።

## ጋብቻ

ስዊዘርላንድ ውስጥ 18 ዓመት ዕድሜ የሞላው ሰው ነው ማግባት የሚፈቀድለት። ተመሳሳይ ጾታ ያላቸው ሰዎችም ማጋባት ይችላሉ። አንድ ወንድ ከአንድ ወንድ ጋር፣ እንደዚሁም አንዲት ሴት ከአንዲት ሴት ጋር መጋባት ይችላሉ። እነሱም እንደ ሌሎች ጥንዶች እኩል መብት አላቸው፣ በዚህም ምክንያት መጋባትም ይፈቀድላቸዋል። መጋባት በሚፈልጉበት ግዜ የነዋሪዎች መመዝገቢያ ጽሕፈት ቤት ማለትም /በሲቪል ማዘጋጃ ቤት/ Basel-Stadt (Zivilstandsamt) ማመልከት አለባቸው። የነዋሪዎች መመዝገቢያ ጽሕፈት ቤቱ የአሰራር ሂደቱን የሚጀምረው (Ehevorbereitungsverfahren)“በጋብቻ ዝግጅት ሂደት“ መሰረት ነው። በዚህ የአሰራር ሂደት ጋብቻው መስመር እንዲይዝ ይደረጋል። ለምሳሌ ያህል ጽ/ቤቱ ሁለቱ ጥንዶች ለመጋባት መስፈርቱን ማሟላታቸውን ያረጋግጣል። የአሰራር ሂደቱ ሲያልቅ ጥንዶቹ በ3 ወራት ውስጥ መጋባት አለባቸው። የነዋሪዎች መመዝገቢያ ጽሕፈት ቤቱ የአሰራር ሂደቱ እንዴት እንደሆነ እና ምን ዓይነት ሰነዶች እንደሚያስፈልጉ መረጃ ይሰጣቸዋል።
ምናልባት አንዳቸው ነዋሪነታቸው ውጪ አገር ከሆነ መጀመሪያ ወደ ስዊዘርላንድ መግባት እንዲፈቀድላቸው ማመልከቻ ማቅረብ አለባቸው (ለመጋባት የሚደረጉ ዝግጅቶች) ። ከዛ በኋላ ሁለቱም እዚህ ስዊዘርላንድ ውስጥ መጋባት ይችላሉ።
የነዋሪዎች መመዝገቢያ ጽሕፈት ቤቱ የይስሙላ ጋብቻ (Scheinehe) ነው ብሎ ጥርጣሬ ሊያድርበት ይችላል። የይስሙላ ጋብቻ (Scheinehe) ማለት: ሁለቱ ጋብቻውን የሚፈጽሙት አንዳቸው ስዊዘርላንድ ውስጥ መኖር እንዲያስችላቸው ብቻ ከሆነ ነው። በዚህም የተነሳ የነዋሪዎች መመዝገቢያ ጽሕፈት ቤቱ ጋብቻውን ውድቅ ሊያደርገው ይችላል። ጋብቻውን ፈጽመው ከሆነም ጽ/ቤቱ ጋብቻውን ውድቅ ሊያደርገው ይችላል። ይህም ማለት ጋብቻው ይፈርሳል ማለት ነው። ምናልባትም በዚህ በይስሙላ ጋብቻ ምክንያት የመቆያ/የመኖሪያ ፍቃዳቸውን ሊያጡ ይችላሉ።

## መብት እና ግዴታዎች

ሁለቱም ባለትዳሮች ተመሳሳይ መብት እና ግዴታዎች አላቸው፣ ይህም በሕግ ላይ በሰፈረው መሰረት ነው። በትዳራቸው ውስጥ እኩል መብት አላቸው። ሁለቱም የትዳር አጋሮች ፈቅደው መጋባት አለባቸው። የግዴታ ጋብቻ (Zwangsheirat) ማለት አንድ ሰው ተገዶ ጋብቻ ሲፈጽም ነው። አስተዳደሩ ይህ እንዳልሆነ ሲያረጋግጥ፣ ትዳሩን ውድቅ ያደርገዋል። አንድ ሰው ሌላውን ሰው በማስገደድ ጋብቻ ፈጽሞ ከሆነ በሕጉ መሰረት ይቀጣል። ተገድደው ያለ ፍቃድዎ ጋብቻ ውስጥ የሚገቡ ሆነው ይሰማዎታል? Beratungsstelle zwangsheirat.ch የሚባለው የግዴታ ጋብቻን በሚመለከት የምክር አገልግሎት የሚሰጠው ተቋም ድጋፍ ያደርግሎታል። በነጻ ስልክ መደወል ይችላሉ፣ አያስከፍልም። የቴለፎን ቁጥሩ እንደሚከተለው ነው፣ 0800 800 007

## የቤተሰብ እቅድ

ስለ ቤተሰብ እቅድ በሚመለከት ጥያቄ አለዎት፣ ማለትም ስለ እርግዝና እና ስለ ጾታ? ይህንን በሚመለከት በ Basel-Stadt ካንቶን የምክር አገልግሎት መስጫ ቢሮዎች አሉ። እነዚህ ቢሮዎች ስለተለያዩ አርእስቶች፣ ለምሳሌ ያህል ስለ ጽንስ መከላከያ፣ ስለ ጾታዊ ችግሮች፣ ስለ ጾታዊ ጤንነት እንክብካቤ፣ ስለ አባለዘር በሽታዎች ወይም ያለ ፍላጎት ስለማርገዝ መረጃ ይሰጣሉ። ልጅ ለመውለድ እየጠበቁ ከሆነ ወይም ልጅ ወልደው ከሆነ ምክር ይለግስዎታል።

## ፍቺ

ባለ ትዳር ነዎት እናም ፍቺ መፈጸም ይፈልጋሉ? የሚፈልጉ ከሆነ ባዝል ከተማ በሲቪል ፍርድ ቤት Basel-Stadt (Zivilgericht) የፍቺ ማመልከቻዎን ማቅረብ አለብዎት። ፍቺውን ብቻዎትን ማቅረብ ይችላሉ፣ ወይም ከትዳር ጓደኛዎ ጋር አንድ ላይ በጋራ ያመልክቱ።
ውጭ አገር ነው የተጋቡት? ቢሆንም እንኳን በስዊዘርላንድ ሕግ መሰረት መፋታት ይችላሉ። ነገር ግን ቢያንስ ከአንድ ዓመት በላይ ስዊዘርላንድ ውስጥ መኖር አለብዎት፣ ከዛ በተጨማሪም ዋና መኖሪያዎ ስዊዘርላንድ ውስጥ መሆን አለበት። ከተፋቱ በፍቺው ምክንያት ምናልባትም መኖሪያ ፍቃድዎ ላይ ለውጥ ሊያመጣ ይችላል። ምናልባትም ከፍቺው በኋላ ስዊዘርላንድ መኖር ሊፈቀድልዎ አይችልም ይሆናል። ዜግነት መውሰድ ይፈልጋሉ? ምናልባትም ከፍቺው በኋላ የስዊዘርላንድ ዜጋ መሆን አይችሉ ይሆናል።
ከፍቺው በኋላ ስዊዘርላንድ መቆየት ይፈቀድሎታል? የጋብቻ እና የቤተሰብ የምክር አገልግሎት ጽ/ቤት ምክር ቢጠይቁ መልካም ነው። የቤት ውስጥ ጥቃት ሰለባ ከሆኑ፣ ይህንን በሚመለከት ልዩ ሕጎች አሉ።

## ተጨማሪ መረጃ ሊንኮች፣ አድራሻዎች፣ በራሪ ወረቀቶች፣ ማብራሪያ ጽሑፎች

www.hallo-baselstadt.ch/am/partnerschaft-und-kinder/partnerschaft